የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ነሃሴ 7 ቀን 2008 ዓ. ም.

**<u>በአውሮፓ የኢሕአፓ አባላት ጉባዔያቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቁ</u>**

በአውሮፓ የኢሕአፓ አባላት ጠቅላላ ጉባዔያቸውን ከነሃሴ 5 ቀን እስከ ነሃሴ 7 ቀን 2008 ዓ. ም. በጀርመን ሀገር፣ በኑረንበርግ ከተማ አካሂደዋል።

ለሶስት ቀን በተካሄደው በዚህ ጉባዔ ላይ ከአውሮፓ ሀገራት የተወከሉ አባላት ተገኝተዋል። ጉባዔውም በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በስፋትና በጥልቀት መርምሩዋል። በተለይም በደልና ጭቆና ከልክ ያለፈበት የኢትዮጵያ ህዝብ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ፆታና ዕድሜ ሳይለይ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን የእምቢታ እንቅስቃሴ በሙሉ ደግፎ፣ የማይሸራረፍ ህዝባዊ አጋርነቱን አረጋግጧል። በትግሉም የወያኔ ሰለባ ሆነው ውድ ህይወታቸውን ለሰጡ የህዝብ ልጆች ታላቅ ከበሬታውን እየገለጸ፣ ለወላጅ፣ ቤተሰብ፣ ዘመዶቻቸውም መጽናናትን ይመኛል። የታሰሩትና ስረየት እየደረሰባቸው ያሉት በህዝብ ትግል እንዲፈቱ፣ በወያኔ ጥይትና ድብደባ የቆሰሉም በቶሎ እንዲያገግሙ ልባዊ ምኞቱ ነው።

ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትንቅንቅ ዘረኛውን ወያኔ በማስወገድ፣ ሁሉንም ያቀፈና ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን የሚሆንበት ሁኔታ ሩቅ አለመሆኑን በመገንዘብ፣ ትግሉ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ፣ ድርጅታዊ ኃይሉን በሁሉም መስክ ለማጠናከር እና ያላሰለሰ ጥረት ለማድረግ ቃል ገብቷል። በመጨረሻም የአስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊነት የሚከታተሉና ድርጅታዊ እንቅስቃሴውን የሚያስተባብሩ አዲስ የአህጉራዊ ኮሚቴ አመራር አባላት በመምረጥ ጉባዔውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያቸንፋል !

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !